

# አልዓዛር ከሞት ተነሳ

- ኢየሱስ አንዳንድ የቅርብ ጓደኞች ነበሩት። ከእነኝህም መካከል አልዓዛርና እሕቶቹ ማርያምና ማርታ ይገኙበታል። የእነኝህን ወዳጆቹን ቤት አዘውትሮ ይጎበኝ ነበር።

- አንድ ቀን የአልዓዛር እሕት ማርታ ወንድሟ መታመሙን የሚገልፅ መልእክት ወደ ኢየሱስ ላከችበት። ኢየሱስ መልእክቱ እንደደረሰው ወዲያው አልመጣም። ቆየ እንጂ! በቆየበት ጊዜም አልዓዛር ሞተ።

- ኢየሱስ በመጨረሻ ወደቢታኒያ ለመሄድ ሲነሳ አልዓዛር ከሞተ አራተኛ ቀን ሆኖታል።
  ማርታ ኢየሱስ መምጣቱን ስትሰማ ልትገናኘው ሮጣ ወጣች። ኢየሱስም ገና በከተማው መግቢያ ላይ ነበር።
  ልክ ኢየሱስን ስታገኘውም "በጊዜ መጥተህ ቢሆን ኖሮ ወንድሜ አይሞትም ነበር፣" አለችው።

- ኢየሱስም፣ "ወንድምሽ እንደገና ይነሳል፣" አላት። ማርታም የመሰላት ኢየሱስ የሚናገው በዘመን ፍፃሜ ስለሚሆን ትንሳኤ ነበር። ኢየሱስ አሁን ሊያደርግ ስላሰበው ነገር የተናተረ አልመሰላትም።

- ኢየሱስ ስለ ትንሳኤ ከነገራት በኋላ አልዓዛር ከሞት እንደሚነሳ እንደምታምን ጠየቃት። እርሷም፣ " አዎን ጌታ ሆይ ወደዚህ አለም የሚመጣው እውነተኛው የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ  አንተ  ነህ፣" አለችው።

- ማርታም እህቷን ማርያምን ለመገናኘት ሮጠች። ማርያምም በክርስቶስ እግር ስር ወደቀች። እርሷም ማርታ የተናገረችውን ተመሳሳይ  ነገር ደግማ ተናገረች። "እዚህ ብትሆን ኖሮ ወንድማችን ባልሞተ ነበር።"  ኢየሱስ እነርሱ ሲያለቅሱ አይቶ እርሱም አለቀሰ።

❈ ከዚያም ኢየሱስ ከማርያምና ከማርታ ጋር አልዓዛር ወደተቀበረበት መቃብር አብረው ሄዱ። የድንጋይ መዝጊያ ያለው ዋሻ ነበር መቃብሩ። ኢየሱስም የድንጋዩን መዝጊያ እንዲከፍቱት አዘዛቸው። ከዚያም ኢየሱስ ወደእግዚአብሔር ከፀለየ በኋላ ፣ “አልዓዛር ተነሳ!” ብሎ ጮኸ። የሞተው አልዓዛርም በጨርቅ እንደተጠቀለለ ከመቃብሩ ወጣ።

❈ ኢየሱስም፣ “የመቃብር ልብሱን አውልቁለትና እንዲሄድ ልቀቁት፣” አላቸው። ማርያምና ማርታ እንዲሁም ወዳጆቻቸው እጅግ በጣም ደስ አላቸው። አልዓዛር እንደገና ሕያው ሆነ፤ ከቤተሰቡ ጋርም ተቀላቀለ። በዚህ ምክንያትም ብዙ አይሁዳውያን በክርስቶስ ኢየሱስ አመኑ።

*የአልዓዛር ከሞት መነሳት ታሪክ የሚገኘው በዮሐንስ ምዕራፍ 11፡ 1 – 46 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com